Seattle Public Utilities

# የ2025-2030 የስትራቴጂካዊ የንግድ እቅድ ዝማኔ

## ዋንኛው ማጠቃለያ

## መልእክታችን ለእናንተ

የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) በየቀኑ አስፈላጊ የውሃ እና ቆሻሻ አገልግሎቶችን ያቀርባል። የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) የተፈጥሮ ሀብቶቻችንን ከአየር ንብረት ለውጥ እና ከብክለት ለመጠበቅ፣ የአገልግሎት ስርዓቶቻችንን በመንከባከብ እና በማህበረሰባችን ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ ቁርጠኛ ነው።

## እቅዳችንን ለምን እያዘመንን እንደሆነ

የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) ስልታዊ የንግድ እቅድ (SBP) በስራችን እንድናተኩር ይረዳናል። ጠንካራ ጎኖቻችንን ይገነባል እና አስፈላጊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ተግባሮቻችንን ይመራል። እያንዳንዱ የንግድ ሥራ ዕቅድ በስድስት ዓመታት ውስጥ የሚጠናቀቅ የታቀደውን ሥራ ይሸፍናል። ከሶስት አመት በኋላ ይዘምናል።

በዚህ የንግድ እቅድ ማሻሻያ ውስጥ፣ ግቦቻችንን እንገመግማለን፣ ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ ያደረግናቸው ዝማኔዎችን እናቀርባለን እና ለወደፊት የመገልገያ ዋጋዎ ላይ ሊደረጉ የሚችሉ ለውጦችን እናሳውቃለን።

## የእኛ ተልዕኮ

የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች ለዛሬ እና ለወደፊት ትውልዶች ውሃ እና ብክነትን በፍትሃዊነት ለመቆጣጠር ከህብረተሰባችን ጋር በመተባበር ጤናማ ሰዎችን፣ አከባቢዎችን፣ እና ኢኮኖሚዎችን ያሳድጋል።

## እይታችን

ማህበረሰብን ያማከለ፣ አንድ ውሃ፣ ዜሮ ቆሻሻ

## የመመሪያ መርሆዎቻችን

ደንበኞች እና ማህበረሰብ

ተመጣጣኝነት እና ተጠያቂነት

ስጋት እና የመቋቋም ችሎታ

ፍትሃዊነት እና ማጎልበት

አገልግሎት እና ደህንነት

# የትኩረት አቅጣጫዎቻችን እና ግቦቻችን

## ትኩረቶቻችን፡- ፍትሃዊ አስፈላጊ አገልግሎቶችን መስጠት

ግቦቻችን እንደሚከተሉት ናቸው፡-

- መስፈርቶችን እና ግዴታዎችን የሚያሟሉ አስተማማኝ፣ እና ጥራት ያላቸው አገልግሎቶችን መስጠት።
- ለሁሉም ማህበረሰቦች በተሻሻሉ አገልግሎቶች ላይ ኢንቨስት ማድረግ

ስልቶቻችን እንደሚከተሉት ናቸው፡-

- ለግንባር መስመር አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች ግብዓቶችን እና መገልገያዎችን በማቅረብ እና መሰናክሎችን በማስወገድ ስራቸው እንዲሳካ ማድረግ።
- አስፈላጊ ለሆኑ አገልግሎቶች ፍትሃዊ ተደራሽነት እንዲኖር ቅድሚያ መስጠት እና መደገፍ።

## ትኩረቶቻችን፡- አካባቢ እና ጤናን ማስተዳደር

ግቦቻችን እንደሚከተሉት ናቸው፡-

- ከውሀ ተፋሰሶቻችን፣ ከተማዎች፣ እስከ ፑጀት ሳውንድ ድረስ የውሃ ግንዛቤን እና የመቋቋም አቅምን ማዳበር።
- እንደገና መጠቀም ፣ ዓላማ መቀየር እና እንደገና ጥቅም ላይ በማዋል ቆሻሻን ለማስወገድ የሚረዳ “ክብ ኢኮኖሚ” “circular economy” ማራመድ።

ስልቶቻችን እንደሚከተሉት ናቸው፡-

- ውሃችንን ለመጠበቅ በእቅዶች፣ ፕሮጀክቶች፣ እና ፕሮግራሞች ላይ ኢንቨስት ማድረግ።
- ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ለመላመድ ከማህበረሰቦች ጋር መስራት።
- የቁሳቁሶችን አጠቃቀም መቀነስ እና የውሃ እና የካርቦን ብክለትን መከላከል።

## ትኩረቶቻችት፡- ለደንበኞቻችንን፣ ማህበረሰቡን፣ እና ሰራተኞቻችንን ስልጣን መስጠት

ግቦቻችን እንደሚከተሉት ናቸው፡-

- ከደንበኞቻችን እና ከማህበረሰቡ ጋር አጋር መሆን።
- ፍትሃዊነትን የሚያራምድ እና ለማህበረሰብ ጥቅሞችን የሚሰጥ ተቋም መሆን።
- በሁሉም ሰራተኞቻችን ላይ ኢንቨስት ማድረግ።

ስልቶቻችን እንደሚከተሉት ናቸው፡-

- ለውጥ የሚያመጣ የመገልገያ እርዳታ ማቅረብ።
- ደንበኞችን ማበረታታት እና መደገፍ።
- በዘር እና በማህበራዊ ፍትህ መምራት። በማህበረሰቦች ውስጥ በትክክል ኢንቨስት ማድረግ።
- ለሁሉም ሰራተኞች ፍትሃዊ የስራ ቦታ መሆን

## ትኩረቶቻችን፡- የመገልገያዎቻችንን የንግድ ልምምዶች ማጠናከር

ግቦቻችን እንደሚከተሉት ናቸው፡-

- የፍጆታ ዋጋዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ማቆየት።
- ንብረቶችን እና አደጋዎችን በአግባቡ ማስተዳደር።
- የመሻሻል ባህል ማዳበር።

ስልቶቻችን እንደሚከተሉት ናቸው፡-

- የተገቡትን ተስፋዎች መጠበቅ።
- የአገልግሎት አቅርቦትን ለማረጋገጥ የጥገና ተቋማትን መጠገን።
- ፈጠራን መደገፍ።

## የወደፊት የመገልገያ ተመኖች

ወጪዎችን ለመጠበቅ የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) መጠን ይጨምራሉ። ወጪን በመቀነስ እና በሀብቶች ላይ ኢንቨስት በማድረግ እና የአገልግሎት ተደራሽነት እንቅፋቶችን በማስወገድ ውጤታማ ለመሆን እነዚህን ጭማሪዎች ዝቅተኛ ለማድረግ እንሰራለን። አደጋን ለመቀነስ እና የህዝብ ተጠቃሚነትን ለመፍጠር፣ ሌሎች የገንዘብ ምንጮችን እንፈልጋለን፣ በብቃት እንገነባለን፣ እና ስርዓቶቻችንን እናስተዳድራለን።

### ተመኖች እንዲጨምሩ የሚያደርጉ ምክንያቶች/ተጽዕኖች

የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች ወጪዎችን፣ አደጋዎችን፣ እና ገቢዎችን በመተንተን ተመኖችን ያዘጋጃል።

የአገልግሎት ዋጋ መጨመርን የምንገድበው በሚከተሉት ነው፡-

- ትልልቅ ውድቀቶችን ለማስወገድ የቆዩ መገልገያዎችን መተካት፣
- ቆሻሻን መቀነስ፣
- ውጤታማነትን ለማሻሻል አዲስ ቴክኖሎጂን መጠቀም፣
- የቧንቧ መስመሮችን፣ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን፣ የፓምፕ ጣቢያዎችን፣ ህንፃዎችን፣ ወዘተ ለማሻሻያ አስቀድሞ እቅድ ማውጣት።
- ገንዘብን በደንብ ማስተዳደር፣
- ዝቅተኛ የኮንትራት ዋጋዎችን መደራደር፣ እና
- ከቦንድ ገበያዎች ገንዘብ የመበደር ወጪን በመቀነስ።

ነገር ግን፣ በርካታ ምክንያቶች ወጪዎችን ሊጨምሩ እና ቁጠባዎችን ሊያካክሱ ይችላሉ። እነዚህም የዋጋ ንረት፣ ደንቦች፣ የእርጅና ሥርዓቶች፣ የወለድ ተመኖች መጨመር፣ እና የኮንትራት ወጪ መስፈርቶችን ያካትታሉ።

### የሶስት ዓመት ተመን መንገድ እና ትንበያ

የየሲያትል የህዝብ መገልገያዎች የስድስት-ዓመት ተመን መንገድ በየሦስት ዓመቱ ይሻሻላል። የ2025-2030 አማካይ አመታዊ የጭማሪ መጠን 4.7 በመቶ ሲሆን፣ ይህም በ2021-2026 4.2 በመቶ ከነበረው ከፍያለ ነው።

*ሠንጠረዥ 1:-* **2025-2030 አማካኝ የመጠን ጭማሪዎች**

| | የታቀደ የተመን መንገድ | | | ሊሆን የሚችል የመጠን ትንበያ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2025 | 2026 | 2027 | 2028 | 2029 | 2030 | **አማካኝ** |
| ውሃ | 2.0% | 2.0% | 6.3% | 3.3% | 6.5% | 3.8% | **4.0%** |
| ቆሻሻ ውሃ | 5.0% | 5.0% | 5.0% | 6.2% | 7.0% | 5.1% | **5.5%** |
| የፍሳሽ ማስወገጃ | 5.0% | 5.0% | 5.1% | 6.6% | 6.3% | 7.2% | **5.9%** |
| ደረቅ ቆሻሻ | 2.5% | 3.1% | 3.4% | 3.4% | 3.8% | 2.5% | **3.1%** |
| **የተዋሃደ** | **3.7%** | **3.9%** | **4.9%** | **5.0%** | **6.0%** | **4.6%** | **4.7%** |

የአማካይ አመታዊ ዋጋ መጨመር በብዙ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡-

- ለሲያትል ከተማ የኪንግ ካውንቲ የቆሻሻ ውሃ ማጣራት ዋጋዎች/ ክፍያዎች መጨመር;
- የዋጋ ግሽበት መጨመር:- እና
- የመተዳደሪያ ደንቦች ዋጋዎች፣ የእርጅና ስርዓቶች፣ የወለድ ተመኖች መጨመር።

## የአዋጁ ተጽእኖ

የመገልገያ ወጪዎችዎ እንዲጨምር መጠበቅ ያለብዎት በዚህ መጠን ነው። የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች በደንበኞቻችን ላይ ያለው የዋጋ ጭማሪ ውጤት ያስባል። ሂሳቦችን/ወጪዎችን ዝቅ ማድረግ አስፈላጊ ነው፣ እና ጭማሪዎች ሊገመቱ የሚችሉ እንዲሆኑ፣ እና ለሚፈልጉ ሰዎች የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ጠንክረን እንሰራለን።

ሠንጠረዥ 2 ለአንድ ቤተሰብ ቤት ደንበኛ የተለመደ ወርሃዊ ወጪ ትንበያ ያሳያል (የ SPU ሂሳቦች በየሁለት ወር የሚከፈሉ ናቸው)።

*ሠንጠረዥ 2*፡- **ለነጠላ ቤተሰብ ቤት የተለመደ ወርሃዊ ወጪ ትንበያ**

| | 2025 | 2026 | 2027 | 2028 | 2029 | 2030 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| *ውሃ* | $50 | $51 | $54 | $56 | $60 | $62 |
| *የፍሳሽ ማስወገጃ* | $83 | $87 | $92 | $97 | $104 | $109 |
| *የፍሳሽ ማስወገጃ** | $63 | $66 | $69 | $74 | $78 | $84 |
| *ደረቅ ቆሻሻ* | $60 | $62 | $64 | $66 | $68 | $70 |
| **የተዋሃደ** | $256 | $266 | $279 | $293 | $310 | $325 |
| **ካለፈው ዓመት ወርሃዊ ለውጥ** | $11 | $10 | $13 | $14 | $17 | $15 |

* *የደንበኞች የውሃ ፍሳሽ ክፍያዎች በኪንግ ካውንቲ ንብረት ታክስ መግለጫዎቻቸው ላይ ይከፍላሉ።*

## የደንበኛ የገንዘብ ድጋፍ

ምንም ያህል ገንዘብ ቢኖርዎትም አስፈላጊ አገልግሎቶችን ማግኘት አለብዎት። ወጪን ዝቅ ለማድረግ ያለን ቁርጠኝነት በጣም አስፈላጊ የሆነው ለዚህ ነው። ነገሮችን ለእርስዎ ቀላል ለማድረግ እንሰራለን። ገንዘብ ለመቆጠብ እንዲያግዝዎት የክፍያ እርዳታ እና ፕሮግራሞችን እናቀርባለን፤ እነዚህንም ጨምሮ፡-

- ***መረጃ*** የመገልገያ ወጪዎችን እንዴት ዝቅ ማድረግ እንደሚቻል
- ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ደንበኞች አስፈላጊ ከሆነ የፍጆታ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ የሚረዳው **የፍጆታ ቅናሽ ፕሮግራም**;
- ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ደንበኞች ያልተከፈሉ ሂሳቦች የሚረዳው **የአደጋ ጊዜ እርዳታ ፕሮግራም**;
- የመገልገያ ክፍያዎችን ለመክፈል ቀላል ለማድረግ የክፍያ እቅዶች **Payment plans** ; እና
- የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች የማህበረሰብ ልገሳ ፈንድ **Community Donation Fund**፣ የ SPU ደንበኞች እርስበርስ እንዲረዳዱ ያስችላቸዋል።

በበለጠ ይወቁ

ሙሉው የ2025-2030 የስትራቴጂክ የንግድ እቅድ ማሻሻያ

https://www.seattle.gov/utilities/about/plans/strategic-business-plan ላይ ይገኛል።